## መ ግ ቢ ያ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ራዕይ፣ ተልዕኮ ዓላማና ግብ ከሁለት መሠረታዊ እውነታዎች ይመነጫል:: አንደኛው የሀገራችን ፍቅር ሲሆን ሁለተኛው እንደህዝብ ያለንን ማህበራዊ እንቅስቃሴ ሊቃኝ ይገባል ብለን የምናምንበት ሚዛናዊና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ነው:: እውነተኛ የሐገር ፍቅርና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ካለ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው እየተሸጋገሩ ለዘመናት አብረውን የኖሩና እየተወሳሰቡ የመጡ ፈርጀ ብዙ ችግሮቻችን በሠላማዊ መንገድ በመነጋገር፣ በመደማመጥና በመግባባት የሚፈቱ ናቸው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ አኩሪ ታሪክ የገፀ-ምድርና የከርሰ ምድር ሀብት እንዲሁም የተፈጥሮ ውበት ያላት ሀገር ናት:: ሆኖም የዚህ አኩሪ ታሪክ፣ ባህልና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት የሆነ ህዝብ በዓለም ህዝብ ፊት የሚታወቀው በርሀብተኝነት፣ በተመጽዋችነት በስደትና በእርስ በርስ ጦርነት ነው::

ዛሬ ኢትዮጵያ በፖለቲካ እድገት ብቻ ሳይሆን በኤኮኖሚ፣ በማህበራዊና በባህላዊ እድገት የዓለም ሀገራት ጭራ ሆናለች:: ሰፊ ሀገር ሆና የባህር-በር የላትም:: ሕዝቧ የዘር፣ የኃይማኖት የቋንቋና የባህል ልዩነቶችን ተቀብሎ ለበርካታ ዘመናት ተቻችሎ የኖረ ቢሆንም ዛሬ እርስ በእርስ በጥርጣሬ እንዲተያይና አንድነቱ እንዲላላ ሆኗል:: በሕገ-መንግሥቱ እውቅና ያገኙ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ማስከበር አልቻለም:: የኤኮኖሚ ዕድገቱም አስተማማኝነትና ቀጣይነት የሌለው በመሆኑ ካለበት የድህነት አዘቅት ሊወጣ አልቻለም:: ፍትሀዊ የሀብት ሥርጭትና የሥራ እድል ባለመኖሩ በኢትዮጵያውያን መሀከል ያለው የኑሮ ደረጃ እጅግ የተራራቀ ሆኗል:: ዜጎች የዜግነት ክብራቸውን አጥተው በሀገራቸው ጉዳይ ባይተወር ሆነዋል::

የፓርቲያችን ራዕይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከውስብስብና ፈርጀ ብዙ ችግሮች ተላቅቆ እያንዳንዱ ዜጋ በነፃነት የማሰብ፣ ሀሳቡን የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ የፈለገውን የመደገፍና ያልፈለገውን የመቃወም፣ በፈለገው ሙያና የሥራ መስክ ተሰማርቶ ሀብት የማፍራትና የሀብቱ ባለቤት የመሆን እንዲሁም የግል ስብዕናውን ማሳደግ የሚችልበት መብቱ ተረጋግጦ ማየት፣ ከድህነት ከኋላ ቀርነትና ከጦርነት የተላቀቀች ሠላም ዴሞክራሲና ፍትህ የሰፈነባት የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባት ነው:: ለዚህ ራዕያችን እውን መሆንም :-

1. ፓርቲያችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊነት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ሥርዓቱን ለመገንባትና ለማራመድ በቁርጥ ይታገላል::

2. በፓርቲው ፕሮግራም ውስጥ ለተካተቱ አንዳንድ ጉዳዮች ተፈፃሚነት ሕገ-መንግሥቱ ባስቀመጠው ሥነ-ሥርዓት መሠረት የሕገ-መንግሥቱን አንዳንድ ድንጋጌዎች ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

3. አሁን ያለው ሕገ-መንግሥት ሊሻሻል የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ እነዚህ መብቶች እንዳይጣሱ የሚከላከሉና ሲጣሱም አስፈላጊውን እርምትና ፍትህ የሚሰጡ ነፃና ገለልተኛ ተቋማት እንዲጠናከሩ ፓርቲያችን ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

4. ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህሎች ቋንቋዎች ወጎችና ሥርዓቶች አሸብርቃ የኖረች በብዙ ዓይነት ሀረጎች ተሳስረውና በታሪክ ተቆራኝተው የጋራ አመለካከትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በማዳበር ለዘመናት ተቻችለውና ተከባብረው በአንድነት የኖሩ የብዙ ብሔረሰቦች ሀገር ናት፡፡ እነዚህ ብሔረሰቦች በየዘመናቱ የተለያየ አስተዳደራዊ በደልና ጭቆና ደርሶባቸዋል፡፡ ዛሬም ቢሆን የብሔረሰቦች ጥያቄ በአግባቡ ተፈትቷል ወይም መብታቸው ተከብሯል የሚል እምነት የለንም፡፡ በመሆኑም ፓርቲያችን ሁሉም ብሔረሰቦች በሀገር ጉዳይ ላይ ተገቢው ድርሻና ገንቢ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በጽናት ይታገላል፡፡

5. ከህጋዊና ሠላማዊ ትግል ስልት ውጭ በሀገሪቱ የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓትን ማስፈን (መገንባት) አይቻልም፡፡ ፓርቲያችን ሠላማዊና ህጋዊ የትግል ስልትን የመረጠው ለዘላቂ ልማት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዐት ግንባታና ለብሔራዊ መግባባት ወሳኝ መሆኑን በማመን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ከባቢ (ምህዳር) ለማስፋት፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ለማድረግ፣ የህግ የበላይነትን ለማስፈን ቁርጠኝነትን የተላበሰና ዘላቂነት ያለው ህጋዊና ሠላማዊ ትግልን ሳይታክቱ ማካሄድ ይጠይቃል፡፡ የሠላማዊ ትግልን ምህዳር ለማስፋት ፓርቲያችን ሳይታክት ጥረት ያደርጋል፡፡ ለዚህም ግብ እውን መሆን የሁሉም በህጋዊና ሠላማዊ ትግል ለመሳተፍ የቆረጡ የፖለቲካ ኃይሎችን ትብብር ይጠይቃል፡፡ የነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች የትብብር መድረክ እንዲፈጠርና የተጀመረም ካለ እንዲጠናከር ፓርቲያችን የበኩሉን ሁሉ ያደርጋል፡፡

በሀገራችን በተለይም ባለፉት ሁለት ትውልዶች በመካከላችን የተፈጠሩት ቁርሾዎችና የተለያዩ በደሎች እርስ በርሳችን በመካሰስና አንዱ ሌላውን በመበቀል ሳይሆን የሕጋዊነት መንፈስን በተላበሰ እርቀ ሠላም መፈታት እንዳለበት ጽኑ አቋም አለን፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሠላም፣ ዴሞክራሲ፣ ፍትህ፣ ልማት፣ እኩልነት፣ ነፃነት፣ የሕግ የበላይነት ግለጽነትና ተጠያቂነት የሚሉትን መሠረታዊ መርሆዎች በመመርኮዝ የፓርቲያችንን ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ የሚገልፀውን ፕሮግራም ዝርዝር እንደሚከተለው አስቀምጠናል፡፡

## 1 . ሐገራዊ ሐቆች፣

**1.1** ሀገረ- ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ገዥነት ስር የሚገኘውን መሬት፣ ውሃ፣ የአየር ክልል ያጠቃልላል::

**1.2** በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው::

**1.3** የኢትዮጵያ ሕዝብም በአገሪቱ ውስጥ ባለሙሉ የሥልጣን ባለቤት ነው፣ ሥልጣንም ከሕዝብ ይመነጫል::

**1.4** የሀገሪትዋ አንድነትም ሆነ ሉዐላዊነት አይነጣጠሉም፣ ለሌላም አይለቀቁም::

**1.5** ኢትዮጵያውያን በግል ያላቸው የዜግነት መብትም ሆነ በወል የሚጋሩት የሕግ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች የአንድነታቸው ዓይነተኛ መሠረት ናቸው::

## 2. የፓርቲው ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማዎች፣

### 2.1 ራዕይ፣

የፓርቲያችን ራዕይ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፣ ድህነት ተወግዶ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ብልጽግናና ፍትህ የሰፈነባት ነፃ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት የተመሠረቱባት ለአለም አቀፍ ሕዝቦች መልካም ግንኙነት የበኩሏን አስተዋጽኦ የምታደርግና የዜጎችዋ ሁሉ አለኝታና መኩሪያ የሆነች ኢትዮጵያን ማየት ነው::

### 2.2 ተልዕኮ፣

የፓርቲያችን ዐብይ ተልዕኮ ራዕያችንን ማሳካት ሆኖ በተለይ ግን በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሠፍንና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ዋስትና ሊሰጥ የሚችል የሕዝብ፣ በሕዝብ ለሕዝብ የቆመ መንግሥት ይመሠረት ዘንድ የሕብረተሰቡን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በሠላማዊ መንገድ በመምራት ለድል ማብቃትና የሕብረተሰቡን ሠላም፣ እድገትና የመኖር ዋስትና ማረጋገጥ ይሆናል::

### 2.3 ዓላማዎች፣

የፓርቲያችን ዐብይ ዓላማ ራዕዩን እውን ለማድረግ የሚረዳው ተልዕኮ መተግበር ሲሆን ጠቅለል ባለ መልኩ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎቹ በሚከተለው ሁኔታ ቀርበዋል:-

**2.3.1** በኢትዮጵያ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበረበት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ማስፈን ፣

**2.3.2** የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች እኩልነት፣ ሀገራዊ አንድነትና ሉዓላዊነት ማስከበር፣

የኢትዮጵያን ዳር-ድንበርና ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ፣

2.3.3 የኢትዮጵያን ህዝብ ከድህነት ኑሮ በማውጣት ልማትንና ማህበራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚረዳ ገበያ መር ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት መገንባት፣

2.3.4 ማህበራዊ ደህንነትን፣ ሠላምን፣ መከባበርንና አብሮነትን፣ ሠርቶ የመኖር ዋስትናን የሚያረጋግጥ ማሕበራዊ ሥርዓት መገንባት፣

2.3.5 የሕግ ልዕልና የተከበረበት ነፃ የዳኝነትና የፍትሕ ሥርዓት ማስፈን፣

2.3.6 ግልጽነትና ተጠያቂነት የሠፈነበት አስተዳደራዊ ሥርዓትን መፍጠር፣ በመንግሥት ተቋማትም ሆነ በሕብረተሰቡ ውስጥ መልካም አስተዳደርን ማጎልበት፣

2.3.7 የሴቶችን፣ የሕፃናትን፣ የአረጋዊያንን፣ የአካል ጉዳተኞችንና ሌሎች ማህበራዊ መገለል የሚደረግባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች መብቶች ማስከበርና ተገቢ እንክብካቤም ማድረግ፣

2.3.8 የብሔራዊ እርቅ መድረክ እንዲፈጠርና የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ብሔራዊ እርቅ በማድረግ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ መታገል፣

2.3.9 ከዓለም ማሕበረሰብ ጋር በመተባበር፣ በመከባበርና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የሀገ ርንና የሕዝብን ጥቅም የሚያስከብር ጤናማና ሠላማዊ ግንኙነት መመሥረት፣

2.3.10 እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግም ፓርቲያችን ዜጎችን በሰፊው ቀስቅሶ እና አሳትፎ ነፃ እና ፍትሀዊ በሆነ ምርጫ ሀገራዊ እና ክልላዊ ስልጣን ለመያዝ ይወዳደራል።

## 3. <u>የፓርቲው የትግል ሥልት፣</u>

3.1 አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ራዕዩን እውን ለማድረግ፣ ተልዕኮውን ለማሳካትና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ህጋዊና ሠላማዊ የትግል ስልቶችን ይጠቀማል፣

3.2 የመንግሥት ሥልጣን መሠረቱ በነፃና ፍትሀዊ ምርጫ አማካኝነት የሚገለጽ የህዝብ መልካም ፈቃድ ሲሆን ድጋፍና ተቃውሞን ለመግለጽ በሕገ-መንግሥቱ እውቅና የተሰጣቸው መብቶች የፓርቲው የትግል ሥልት አካል ይሆናሉ፣

3.3 ሀገራዊ የትግል አንድነትን ለማጠናከር በዴሞክራሲያዊና ሠላማዊ መንገድ ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር የተለያዩ የትግል ግንኙነቶችን ሊፈጥር ይችላል፤ ማንኛውም የፖለቲካ ልዩነት በሠላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈታ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።

## 4. <u>የፓርቲው ርዕዮተ ዓለም፣</u>

አንድነት በግለሰብ ነፃነት ላይ በተመሠረተ የዴሞክራሲ መሠረታዊ መርሆዎችና ፍልስፍና ይመራል። ሆኖም ከሶሻል ዴሞክራሲና ከስምምነት (ከኮንሴንሰስ) ዴሞክራሲ አመለካከቶች መካከል ለሀገራችን እድገትና ብሔራዊ ግንባታ ጠቃሚ የሆኑ እሴቶችንም ይቀበላል።

## 4.1 የፖለቲካ መርሆዎች፣

### 4.1.1 የፖለቲካ ሥርዓቱ አደረጃጀት፣

ሀ/ የፖለቲካ ሥርዓቱ ሕገ-መንግሥታዊና መድብለ ፓርቲ ይሆናል፣

ለ/ የመንግሥት የፖለቲካ ሥልጣን የሚገኘው በነፃና ፍትሐዊ የምርጫ ውድድር ሆኖ ከሕዝብ ፈቃድ የሚመነጭና በሕግ የበላይነት የሚመራ ይሆናል፣

### 4.1.2 የመንግሥት አደረጃጀት፣

ሀ/ የመንግሥት አደረጃጀት ፌዴራላዊ ይሆናል፡፡

ለ/ የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን በሕግ አውጪው፡ በሕግ ተርጓሚውና በሕግ አስፈፃሚው አካላት መካከል የሚከፋፈል ሲሆን አንዱ በሌላው የሥራ ድርሻ ጣልቃ ሳይገባ በእኩልነትና በነፃነት እንዲሰሩ ይደረጋል፣

ሐ/ ሕግ አውጪው አካል ሁለት ክፍሎች /የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴራሉ አካላት ተወካዮች/ የሚኖሩት ሲሆን ሁለቱም ክፍሎች ሕግ የማውጣት የጋራ ሥልጣን ይኖራቸዋል፣

መ/ የዳኝነት አካሉ ከህግ አውጪውና ከህግ አስፈፃሚው ተጽዕኖ ነፃ ሆኖ ይሠራል፡፡ ሕግ የመተርጎም ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ይሆናል፣

ሠ/ ሕግ አስፈፃሚው አካል በቀጥታ በሕዝብ በሚመረጥና የሥልጣን ዘመኑ በሕግ በተገደበ ፕሬዚዴንት የሚዋቀር ይሆናል፣ ፕሬዚዴንቱ የሚመረጠው ለአምስት ዓመት ሆኖ በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

ረ/ በሕግ አስፈፃሚው አካል ሥር የሚዋቀረው ሲቪል ሰርቪስ ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆነ መንገድ በችሎታና ብቃት ላይ ተመስርቶ በግልጽነትና በተጠያቂነት መንፈስ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት በሚችልበት ሁኔታ ይደራጃል፡፡

### 4.1.3 የፌዴራል አወቃቀር፣

ሀ/ የፌዴራል አወቃቀሩ እንደ ሁኔታው መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሠፋፈርን፣ አስተዳደራዊና የልማት አመችነትን፣ ቋንቋን፣ ባህልን፣ ታሪክንና ሌሎች ማህበራዊ ትስስሮችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፣

ለ/ የፌዴራል መንግሥቱና የክልል መንግሥታት በሕግ የተወሰነ የሥልጣን ክልል የሚኖራቸው ሲሆን አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ይደረጋል፣

ሐ/ የራስ አስተዳደር መንግሥታት ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው በመተባበርና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ይኖራቸዋል፣ ፌዴራል መንግሥቱም የዚህ አይነቱ ግንኙነት እንዲጠናከር ያበረታታል አስፈላጊውን እገዛም ያደርጋል፣

መ/ አማርኛ የፌዴራል መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል:: እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በሕዝብ ውሳኔ ሲጸድቅ ሌላ ተጨማሪ የሥራ ቋንቋ እንዲኖር ይደረጋል፣

ሠ/ የራስ አስተዳደር መንግሥታት የሥራ ቋንቋ የክልሉ ህዝብ በሚያደርገው ህዝበ ውሳኔ መሠረት እንዲሆን ይደረጋል::

ረ/ በፌዴራል አከላለል ሂደት ውስጥ የማያግባባ ሁኔታ ሲፈጠር በህዝበ ውሳኔ ይፈታል::

ሰ/ የራስ መንግሥታት የየራሳቸው ሕግ አውጭ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈፃሚ አካላት የሚኖራቸው ሲሆን ከዚያም በታች በየደረጃው ህዝቡ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱን የሚያረጋግጥባቸው ም/ቤቶች ይኖራሉ::

## 4.1.4 ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣

ሀ/ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ያፀደቀቻቸው አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ፖለቲካዊ፣ የሲቪል፣ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ የባሕል፣ የሴቶች፣ የህፃናትና ሌሎች ስምምነቶች የሀገሪቱ የሕግ አካል የሚደረጉ ሲሆን እነዚህም እንዲከበሩና እንዲተገበሩ የሚያስችሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ይደርጋል፣

ለ/ የዜጎች ከቦታ ቦታ የመዘዋወር በፈለጉበት ቦታ የመሥራትና የመኖር፣ በግልና በጋራ ንብረት የማፍራት፣ የመጠቀም፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ መብቶች ይከበራሉ፣

ሐ/ ዜጎች በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ሰልፍ የማድረግ፣ ሥራ የማቆም ወዘተ መብቶች ይከበራሉ፣

መ/ ዜጎች በአዕምሮም ሆነ በአካል ላይ የሚደረጉ ጥቃቶችና መሰቃየቶች እንዳይደርስ ባቸው ይጠበቃሉ፣ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝም አይታሠሩም፣ አይመረመሩም፣ ቤታቸው፣ ሰውነታቸውና ንብረታቸው አይፈተሽም::

## 4.1.5 የብሔረሰቦች እኩልነት፣

ሀ/ ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔረሰቦች ሀገር እንደመሆንዋ መጠን ምንም ዓይነት አድልዎ ሳይፈፀምባቸው እኩልነታቸው ተረጋግጦ የሚኖሩባት ሀገር ትሆናለች፣

ለ/ ሁሉም ብሔረሰቦች ማንነታቸው ተከብሮ በቋንቋቸው የመጠቀም፣ እንዲሁም ባህሎቻቸውንና እምነቶቻቸውን የማበልፀግ መብቶቻቸው ይከበሩላቸዋል፣

ሐ/ ከላይ በ4.1.3 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉም ብሔረሰቦች በሀገሪቱ ሀብት እንዲሁም በትምህርት፣ በጤና በሥራና በሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድሎች እኩል ተጠቃሚ ይሆናሉ፣

መ/ በቁጥር በዛ ካሉ ብሔረሰቦች ጋር ተቀላቅለው ለሚኖሩ በቁጥር አናሳ ለሆኑ ብሔረሰቦች ደህንነትና እንዲሁም የኢኮኖሚና የፖለቲካ መብቶቻቸው ልዩ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፣

ሠ/ ሁሉም ብሔረሰቦች ወደ ተመጣጣኝ የእድገት ደረጃ እንዲደርሱ በእድገት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

### 4.1.6 የፆታ እኩልነት፣

ሀ/ በሀገራችን ለዘመናት ሰፍኖ የኖረውን ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የማየት በፆታዎች መካከል ያለን የተዛባ ግንኙነት በማስተካከል የፆታዎች እኩልነት ይረጋገጣል፣

ለ/ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎና የአመራር ሰጪነት ሚና ይበልጥ እንዲጎለብትና እንዲዳብር ተገቢ እገዛና ድጋፍ ይደረጋል፣

ሐ/ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ በጤና፣ በትምህርትና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ያላቸው ተሳትፎ እንዲያድግ ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

### 4.1.7 የኃይማኖት ነፃነትና እኩልነት፣

ሀ/ ማንኛው ዜጋ የፈለገውን ኃይማኖት የመከተል፣ የማራመድና የማስፋፋት መብትና ነፃነት ይኖረዋል ፣

ለ/ በኢትዮጵያ ያሉ ኃይማኖቶች ሁሉ እኩል ናቸው፣ መንግሥትና ኃይማኖት የተለያዩ ናቸው፣ አንዱ በሌላው ተግባር ጣልቃ እንዲገባ አይፈቀድም።

### 4.1.8 የመደራጀት መብት፣

ሀ/ ዜጎች በሚያምኑበት የፖለቲካ ፓርቲ የመደራጀት መብት አላቸው።

ለ/ በግልና በመንግሥት ተቋማት የሚሠሩ ዜጎች የጋራ ጥቅምና መብቶቻቸውን ለማስከበር በማህበር ተደራጅቶ የመንቀሳቀስ መብታቸው የተከበረ ይሆናል፣

ሐ/ በተለያየ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎችም ሙያቸውን ለማሳደግ ለሀገርና ለህዝብ የሚጠቅሙ አገልግሎቶችን ለማበርከት እንዲሁም ከሙያቸው ጋር የተያያዙ መብቶቻቸውን ለማስከበር በማህበር የመደራጀት መብት ይኖራቸዋል፣

መ/ የተለያዩ የልማት፣ የተራድኦና የግብረሰናይ ማህበራት በነፃነት ተቋቁመው ለአገርና ለህዝብ ተጨባጭ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

ሠ/ ሴቶች ካሉባቸው የፆታና የባህል ተጽዕኖዎች ለመላቀቅ፣ በተለያዩ የፆታ ጉዳዮች ላይ ለመወያየትና ከፆታ ጋር የተያያዙ ልዩ መብቶቻቸውን ለማስከበር በማህበር በነፃ የመደራጀት መብት ይኖራቸዋል፣

ረ/ ወጣቶች በስፖርት፣ በኪነ-ጥበብና በሌሎች የፈጠራ መስኮች እንዲሁም የሀገር ተረካቢነት ብቃታቸውን ማዳበር በሚችሉበት ሁኔታ ተደራጅተው የመንቀሳቀስ መብት ይኖራቸዋል።

### 4.1.9 <u>መገናኛ ብዙኃን ፣</u>

ሀ/ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት ከመንግሥት ቁጥጥርና ተጽእኖ ነፃ ሆነው ትክክለኛ ሕዝባዊ አገልግሎቶች እንዲሰጡ ይደረጋል፣

ለ/ ዜጎች ሃሳባቸውን የመግለጽና መረጃ የማግኘት መብታቸው ይከበራል፣

ሐ/ የግል መገናኛ ብዙኃን እንዲቋቋሙ ይፈቀዳል፣ ተገቢው የሕግ ጥበቃም ይደረግላቸዋል፣

መ/ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆኑ አካላት ይተዳደራሉ፣ በተግባራቸውም ለሁሉም ወገን ክፍት ይሆናሉ፣

ሠ/ ጋዜጦች፣ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ሌሎች ብዙኃን መገናኛ ዘዴዎች የመንግሥትን አሠራር ያለ ፍርሃትና መሸማቀቅ እንዲዘግቡና እንዲተቹ ብሎም ገንቢ አስተያየት እንዲሰነዝሩ ይበረታታሉ።

## 4.2 <u>የኢኮኖሚ መርሆዎች፣</u>

### 4.2.1 <u>አጠቃላይ፣</u>

ሀ/ ለሀገሪቱ ልማትና ብልጽግና ትኩረት የሚሰጥ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃና ማህበራዊ ህይወት የሚያሻሽል ዘላቂና ሁለንተናዊ የእድገትና የልማት ስትራቴጂ ተቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል። ለዜጎችዋ ሥራ መፍጠር የኢኮኖሚው ፖሊሲ ዋነኛ መርህ ይሆናል።

ለ/ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና ጥቅምን ያገናዘበ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት ይገነባል፣

ሐ/ የአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት መሠረት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ስለዚህም የኢኮኖሚው ፖሊሲ ትኩረት ሀገራዊ የኢኮኖሚ ኃይሎችን መፍጠርና ማጠናከር ይሆናል፣የአገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ አስፈላጊ ስለሆኑ የውጪ ባለሀብቶችና እርዳታ ሰጪዎች ይበረታታሉ፣

መ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገው ሙያና የሥራ መስክ የመሰማራት፣ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ሀብትን የማፍራት፣ የመያዝ፣ የመጠቀምና በህጋዊ መንገድ ለሌላ ወገን የማስተላለፍ መብቱ ይረጋገጥለታል፣

ሠ/ የማንኛውም ዜጋ ንብረት አይወረስም ሆኖም መንግሥት በግል የተያዘን ሀብት ለህዝብና ለሀገር ጥቅም ማዋል ሲያስፈልገው በወቅቱ የገበያ ዋጋ ላይ የተመሠረተ ካሳ ወዲያወኑ በመክፈል ማስለቀቅ ይችላል።

ረ/ የአካል ጉዳተኞች በኢኮኖሚው ውስጥ ሙሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስልት ይቀይሳል፣

ሰ/ የልማት ስትራቴጂውም ሆነ የኢኮኖሚ ፖሊሲው የተፈጥሮ ሀብትንና አካባቢን ከመንከባከብና በአግባቡ ከመጠቀም መርህ ጋር የተቆራኙ ይሆናሉ፡፡

### 4.2.2 የኢኮኖሚ ዘርፎች፣

ሀ/ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገት ሀገራዊ መሠረት ሊኖረው የሚችለው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች እድገት ሲዳብር በመሆኑ ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

ለ/ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ካሉበት ችግሮች ተላቆ ምርታማነቱና ዕድገቱ እንዲጨምር ይደረጋል፣

ሐ/ አርብቶ አደሩ ህብረተሰብ ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ወደ ተሻለ፣ አስተማማኝና የተረጋጋ ሕይወት የሚሸጋገርበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

መ/ በገጠርም ሆነ በከተማ ሥራ አጥነት፣ ድህነት በተለይም የምግብ እጥረት ችግርን ለመቅረፍ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል፣

ሠ/ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ እንደ ፋብሪካ፣ አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ቱሪዝም የመሳሰሉት በጠቅላላ ኢኮኖሚው ውስጥ ለወደፊቱ የሚኖራቸው ድርሻም ሆነ ምርታማነታቸው በከፍተኛ ሁኔታ የሚያድግበት ሥልት ተቀይሶ ተግባራዊ ይደረጋል፣

ረ/ የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲያድግና ለጠቅላላ ኢኮኖሚው የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የተጠናከረ እንዲሆን በዘመናዊ መንገድ ይደራጃል፣

ሰ/ ባንክ፣ ኢንሹራንስ፣ የካፒታል ገበያ፣ ልዩ ልዩ የብድር ተቋማትና የመሳሰሉት የፋይናንስ አገልግሎቶች የተረጋጋና ፈጣን እድገት ማስመዝገብ የሚችል ኢኮኖሚ እውን እንዲሆን የሚያግዙና በውድድር ሥርዓት የሚመሩ ሆነው ይደራጃሉ፣ ፋይናንስ፣ ኢንፎርሜሽንና ኰሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት አይነተኛ መሣሪያዎች በመሆናቸው የውጪ ካፒታል ከመንግሥትም ሆነ ከግል ባለሀብቶች ጋር በመቀናጀት ወይም ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት የውጪ ኢንቨስትመንት በተናጠልም ቢሆን በዚህ ዘርፍ እንዲሳተፍ ይደረጋል፡፡

ሸ/ ለኢኮኖሚው እድገት አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶች እንዲገነቡና እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣

ቀ/ ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ስለዚህም የልማት ፕሮጀክቶች ሲታቀዱም ሆነ ሲገነቡ የአካባቢ ችግር እንዳያስከትሉ ጥንቃቄና ክትትል ይደረጋል፣

በ/ የሀገሪቱን ባህልና የሞራል እሴቶች በጠበቀ መልኩ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ የግል ባለሀብቶች በዚህ የኤኮኖሚ ዘርፍ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፡፡

## 4.3 የመሬትና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤትነት፣

ሀ/ ለመንግሥት አገልግሎት የሚውል ካልሆነ በቀር ማንኛውም የገጠር መሬትና የከተማ ቦታ የኢትዮጵያውያን የግል ሀብት ይሆናል፣

ለ/ እያንዳንዱ የመሬት ባለቤት መሬቱን የማልማት፣ የመንከባከብ፣ የማከራየት፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ በውርስ ወይም በስጦታ ለሌሎች የማስተላለፍ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ይሆናል፣

ሐ/ ማንኛውም ሰው በግል ባለቤትነት የያዘው መሬት ለመንግሥት አገልግሎት ቢፈለግ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ላይ የተመሠረተ ካሣ ለባለቤቱ እንዲከፈለው ይደረጋል፣

መ/ የግጦሽ መሬቶች፣ ለማህበራዊ አገልግሎት የተከለሉ ቦታዎች፣ አውራ መንገዶችና የአርብቶ አደሩ የግጦሽ አካባቢዎች በህዝብ የወል ንብረትነት ይያዛሉ፣

ሠ/ ሕዝብ ያልሰፈረባቸውና ገና ያልለሙ መሬቶች በሂደት ለህዝብ እስከሚደለደሉ ድረስ በመንግሥት ይዞታ ሥር ሆነው በኪራይና በገደብ ለባለሀብቶች እየተሰጡ የሚለሙበት ሁኔታ ይፈጠራል፣

ረ/ ሐይቆች፣ ወንዞችና ጅረቶች፣ ተራራዎች፣ ሰፋፊ ደኖች፣ ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳትና ማዕድናት በመንግሥት ይዞታ ሥር ሆነው አስፈላጊውን ጥቅምና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ ያካባቢው ሕዝብ ተጠቃሚነትም ከግምት እንዲገባ ይደረጋል።

ሰ/ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻችንን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ አቅምን ለመገንባት ጥረት ይደረጋል፤ የውሃ ሀብታችንን ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ከሌሎች የተፋሰስ ሀገሮች ጋር የሚደረጉ ውይይቶችና ትብብሮች ውጤታማ እንዲሆኑ የበኩላችንን ጥረትና አስተዋጽኦ እናደርጋለን።

### 4.3.1 የመንግሥት ሚና ፣

ሀ/ የአሠሪና ሠራተኛ መብቶችና ግዴታዎችን በግልጽ የሚያስቀምጡ የኢኮኖሚ ነፃና ፍትሐዊ ውድድር የሚያዳብሩ የንብረት ባለቤትነት መብትን የሚያረጋግጡና ሌሎች ለኤኮኖሚው አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ ሕጎችንና መመሪያዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ/ ለኢኮኖሚው ጤናማ እድገት የፖለቲካ መረጋጋትና የሠላምና ደህንነት መኖር አስፈላጊ በመሆኑ ይህንኑ እውን ለማድረግ መንግሥት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣

ሐ/ ለኢኮኖሚ እድገት አጋዥ የሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በመመሥረት መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ሙስናን ለመታገል መንግሥት ትኩረት ይሰጣል፣

መ/ ከፍተኛ የሥራ አጥነት ሲከሰት፣ የኢኮኖሚ መቀርቀዝ ሲያጋጥም፣ የዋጋ ግሽበት ሲመጣ፣ የመንግሥት የበጀት ጉድለት ሲጨምር እና መሰል ችግሮች ሲከሰቱ መንግሥት የማረጋጋት እርምጃ ይወስዳል፣

ሠ/ ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቅ፣ አዋጪነቱ አጠያያቂ ወይም የሚያስገኘው ጥቅም ከረዥም ጊዜ በኋላ ሲሆን ወይም ተፈላጊነቱ ስትራቴጂካዊ በመሆኑና በመሳሰሉት ምክንያቶች መንግሥት ከግሉ ጋር በሽርክና ወይም ለብቻው የልማት ድርጅቶችን አቋቁሞ ያስተዳድራል፣ ሆኖም አዋጪነታቸው አስተማማኝ የሆኑትን ወይም በግል ይዞታ ቢሆኑ የተሻለ ውጤት የሚኖራቸውን የልማት ድርጅቶች ወደ ግሉ ይዞታ ወይም አስተዳደር ሥር እንዲዛወሩ መንግሥት እርምጃ ይወስዳል፣

ረ/ ለግለሰቦችና ለድርቶች በልዩ ልዩ መንገድ መንግሥት ድጋፍና እርዳታ ያደርጋል።

### 4.3.2 የውጭ ባለሀብቶች ሚና፣

ሀ/ ኢትዮጵያ በጣም ደሀ ከሚባሉት ሀገራት አንዷ እንደ መሆንዋ በሐገሪቱ ዘላቂ እድገት ለማምጣት የውጪ ኢንቬስትሜንት ለመሳብ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል።

ለ/ ከሀገሪቱ ጥቅሞችና ከሀገራዊ ባለሀብቶች ሥራ ጋር በማይጋጭ ሁኔታ የውጭ ባለሀብቶች በኢኮኖሚው እንቅስቀሴ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፣

ሐ/ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን፣ የሥራ ልምድንና ዕውቀትን በስፋት ወደ ሀገር ማስገባት ለሚችሉ የውጭ ባለሀብቶች ልዩ ድጋፍ ይደረጋል፣

መ/ የውጭ ባለሀብቶች የሚሠማሩበት ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በውጭ ሀገር ዜጎች እንዲሸፈን ሊያደርጉ ይችላሉ። ሆኖም ግን የውጭ ባለሀብቶች የውጭ ዜጎችን ማሠራት ቢችሉም በሂደት ግን ኢትዮጵያውያንን በማሠልጠን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል።

## 4.4 የማህበራዊ መርሆዎች፣

### 4.4.1 አጠቃላይ፣

ሀ/ ሀገራዊ ስሜቱ የጎለበተ፣ በብሔራዊ ማንነቱ የሚኮራ፣ በአካልም ሆነ በአዕምሮ የዳበረና የሥራን ክቡርነት የተገነዘበ ብርቱና ጤናማ ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችሉ የትምህርት፣ የጤናና የባሕል ፖሊሲዎች ይቀረፃሉ፣

ለ/ ዜጎች ያለምንም አድልዎ በሀገራቸው ማህበራዊ ልማት ውስጥ እኩል የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል፣

ሐ/ የዜጎች ማሕበራዊ ደህንነት፣ ሠላም፣ መከባበር፣ አብሮነትና የሥራ ዋስትና ይረጋገጣሉ፣

መ/ የዜግነት ክብርን፣ ሠላም፣ ማሕበራዊ ሕይወትንና የእምነት ነፃነትን የሚያረጋግጥ ማሕበራዊ ሥርዓት ይገነባል፣

ሠ/ ቤተሰብ የማህበረሰብ መሠረት በመሆኑ ልዩ የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል።

### 4.4.2 ትምህርት፣

ሀ/ ተግባር ተኮርና ጥራት የለው ትምህርት ለዜጎች ይሰጣል:: የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና የሥነ-ጥበባት ትምህርት ይበረታታል:: በተለይ የፈጠራ ችሎታ ላላቸው ዜጎች ልዩ ድጋፍ ይደረጋል፣

ለ/ የትምህርት ሽፋን በሁሉም አካባቢዎች እንዲሁም በከተማና በገጠር ፍትሐዊ ስርጭት እንዲኖረውና የሴቶች ተሳትፎ እንዲጨምር ይደረጋል፣

ሐ/ ዜጎች እስከ ሁለተኛ ደረጃ ፍፃሜ የሚሰጠውን ትምህርት በመንግሥት ትምህርት ቤት ከክፍያ ነፃ የመማር መብት ይኖራቸዋል:: ከዚያ በላይ ያለውን ትምህርት እንደአስፈላጊነቱ ተማሪዎች ከወጪው እንዲጋሩ ሊደረግ ይችላል፣

መ/ በትምህርት ሥራ የግል ባለሀብቶችም በሁሉም ደረጃ እንዲሳተፉ ይደረጋል:: የትምህርትን ጥራት የመጠበቅ ኃላፊነት የመንግሥት ይሆናል፣

ሠ/ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በትምህርትና በሥልጠና በተለይ በአማራጭ የመሠረት ትምህርትና በአፀደ ህፃናት ትምህርት መስክ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፣

ረ/ ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ዜጎች እንዲሁም ማህበራዊ መገለል የሚደረግባቸው ማሕበረ ሰቦች የትምህርት ተሳትፎአቸውን እንዲያጎለብቱ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፣

ሰ/ የትምህርትን ሥራ አተገባበርና የሥርዓተ ትምህርቱን አደረጃጀት ግልጽ የሚያደርግ የትምህርት ፖሊሲ በመምህራን፣ በትምህርት ባለሙያዎች በተማሪዎች፣ በወላጆችና በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ተሳትፎ ይቀረፃል፣

ሸ/ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ላይ ሕፃናት አፍ በፈቱበት ቋንቋ የመማር መብታቸው ይጠበቃል::

ቀ/ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ከአንደኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ይሰጣል፣ ማንኛውም ቤተሰብ ልጁን ወይንም በሥሩ የሚገኙ ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት በመላክ እስከ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የማስተማር ግዴታ አለበት፣

በ/ ከመደበኛ ትምህርት ጎን ለጎን ሙያ-ነክ የጎልማሶች የትምህርት መስክ እንዲስፋፋና መኃይምነት ከሀገሪቱ እንዲጠፋ ልዩ ትኩረት ይሰጣል::

### 4.4.3 ጤና ፣

ሀ/ በሽታን በመከላከል መርህ ላይ የተመሠረተ የጤና ፖለሲ ይቀረፃል፣

ለ/ በወረርሺኝ መልክ የሚሰራጩ እንደ ሳምባ ነቀርሳ፣ ወባና ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የመሳሰሉ በሽታዎችን ለመግታት ተግባራዊና ትምህርታዊ እንቅስቃሴ ይደረጋል፣

ሐ/ ዜጎች በያሉበት አካባቢ የጤና አገልግሎትን እንዲያገኙ ይደረጋል፣

መ/ በጤናው ዘርፍ መንግሥት ወሳኝ ድረሻ ቢኖረውም የግል ባለሀብቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጤና ዘርፍ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ::

## 4.4.4 ማህበራዊ ደህንነትና የሥራ ዋስትና፣

ሀ/ የዜጎች ሠርቶ የመኖር መብት የተከበረ ነው:: ስለዚህም የሥራ ባህል እንዲዳብር አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል፣

ለ/ ሥራ አጥነትና ድህነትን ለመቅረፍ መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የግል የኤኮኖሚ ዘርፍና ሕብረተሰቡ በተናጠልም ሆነ በቅንጅት እንዲሠሩ ይደረጋል፣

ሐ/ መንግሥት የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ ረዳት የሌላቸው አረጋውያንን፣ ወላጅ አልባ ሕፃናትንና ጡረተኞችን ለመንከባከብ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል::

## 4.4.5 ባሕልና ባሕላዊ ዕሴቶች ፣

ሀ/ የሀገሪቱ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ባህሎችና ባህላዊና ኃይማኖታዊ ታሪካዊ ቅርሶች የሕግ ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፣

ለ/ ኢትዮጵያውያን ይበልጥ እንዲቀራረቡና የጋራ ብሔራዊ ስሜታቸውን እንዲያጎለብቱ ባህላዊ ቅርሶቻቸውና ዕሴቶቻቸውን እንዲያውቁና እንዲያከብሩ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል::

## 4.5 ፍትሕ፣

ሀ/ ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት እኩል ነው:: ማንም ግለሰብ ሆነ ድርጅት ከሕግ በላይ ሊሆን አይችልም::

ለ/ ዜጎች በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ፍትሕ የተረጋገጠበት ሕይወት እንዲኖራቸው ይደረጋል::

## 4.6 ስፖርትና ኪነ-ጥበብ፣

በአካልና በመንፈስ የዳበረ ጠንካራ ዜጋን ለመፍጠር ስፖርትና ኪነ-ጥበብ ትኩረት ይሰጣቸዋል:: በመንግሥትና በግል ባለሀብቶች እንዲሁም በሕዝብ ትብብር ስፖርትና ኪነ-ጥበብ እንዲስፋፋና እንዲዳብር ጥረት ይደረጋል::

## 4.7 የውጭ ግንኙነት ፣

ሀ/ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የብሔራዊ ጥቅሞች ማራመጃ መሣሪያ ሲሆን ከማንኛውም ሀገርና መንግሥት ጋር በእኩልነት፣ በጋራ ጥቅም በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል:: በተለይ ከጎረቤት አገሮች ጋር ቅርበት ያለው የወዳጅነት፣ የትብብር፣ የመተጋገዝና የጋራ እድገት ግንኙነቶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ጥረት ይደረጋል፣

ለ/ ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች ይከበራሉ፣

ሐ/ በውጪ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርና ጥረው ግረው ያፈሩት ሀብታቸው እንዲጠበቅ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል። የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

መ/ ከኢትዮጵያ አቢይ የውጭ ጉዳዮች በቀዳሚነት የሚታየው የኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤትነት ጥያቄ ሠላማዊና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲረጋገጥ ጽኑ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ይደረጋል።

## 4.8 መከላከያ፣

ሀ/ ለህገ መንግሥቱ ተገዢና ከየትኛውም ፓርቲ ነፃ የሆነ፣ በሕዝብ የመብት ጥያቄ ላይ ጣልቃ የማይገባ፣ ለኢትዮጵያ ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት መጠበቅና ለሕዝቡ ሠላምና ደህንነት መከበር የቆመ ብሔራዊ የመከላከያ ኃይል ይኖራል፣

ለ/ የመከላከያ ኃይል በጥንቅሩ ከሁሉም የሕብረተሰቡ ክፍሎች የተውጣጣ ሆኖ በሎጂስቲክስና በዘመናዊ መሣሪያ የተጠናከረ፣ የሙያ ብቃት ያለው፣ ዘመናዊና ግዳጁን ለመወጣት ዝግጁ የሆነ ሠራዊት እንዲኖረው ይደረጋል፣

ሐ/ የመከላከያ ኃይል አባላት በዜግነት መብታቸው የመምረጥና ከሠራዊቱ እስከ ለቀቁም የመመረጥ መብታቸው የተከበረ ነው፣

መ/ ከመደበኛ ሠራዊቱ ውጪ ተጠሪነታቸው ለአካባቢው መስተዳድር የሆነ፣ ህዝቡ የአካባቢውን ሠላም በማስከበርና ሀገሩን ከማናቸውም ጥቃት በመከላከል ረገድ የነቃና የተደራጀ የሚሊሺያ ተሣትፎ እንዲኖረው የሚያስችል ጥረት ይደረጋል። ሆኖም በዚህ መልክ የሚቋቋሙ የሚሊሺያ ኃይሎች እንደ መከላከያ ኃይሉ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ነፃ ይሆናሉ። ሥልጠናቸው ዘመናዊ መሆኑ፣ አባላቱም በሥነ-ምግባር የታነፁና ለሕግ ተገዥ መሆናቸውን ፌዴራል መንግሥቱ ይከታተላል።

## 4.9 ፖሊስ ፣

ሀ/ የህዝብን ሠላማዊ ኑሮ የሚያስከብር ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ የሆነ የፖሊስ ኃይል ይኖራል። በጥንቅሩም ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ሆኖ ሕዝብን ለማገልገል የሚያበቃ ሥነ-ምግባር የተላበሰና ህግና ፍትህን ለማስፈፀም የሚያስችል ጥራትና የሙያ ብቃት ያለው ኃይል እንዲሆን ይደረጋል፣

ለ/ የፖሊስ ኃይሉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ ጋር አይወግንም። ነገር ግን በዜግነት መብታቸው አባላቱ የመምረጥና ከፖሊስ ኃይሉ እስከለቀቁ ድረስ የመመረጥ መብት ይኖራቸዋል።

ሐ/ እያንዳንዱ የራስ አስተዳደር ክልል መንግሥት ለክልሉ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት ጥበቃ በሕግ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት የፖሊስና የአካባቢ ጥበቃ ኃይል ያቋቁማል።

## 4.10 ደህንነት ፣

ለሲቪል መስተዳደሩ ተጠሪ የሆነና የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለው የሀገርና የሕዝብን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለው የሰለጠነ የደህንነት ተቋም በፌዴራል ደረጃ ይቋቋማል፡፡

# አንቀጽ 5 ነፃ ተቋማትን የመመሥረት አስፈላጊነት

በሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያለነፃ ተቋማት ህልውና ተግባራዊ ሊደረግ ስለማይቻል፡-

ሀ / ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ለ/ የፀረ-ሙስና ተቋም

ሐ/ የሰብአዊ መብት ኰሚሽን

መ/ የእንባ ጠባቂ ተቋም

ሠ/ የዋናው ኦዲተር መስሪያቤት እና የመሳሰሉት ከማንኛውም የመንግሥት አካል ጣልቃ ገብነትና ተጽዕኖ ነፃ ሆነው በገለልተኝነት እንዲዋቀሩና እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡